# የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያ

**የሽማግሌ ምትክ ምርጫ**

የሽምግልና አገልግሎት ዘመኑን በሚጨርሰው በወንድማችን ሲሳይ መሸሻ ምትክ ሽማግሌ ለመምረጥ ጥቆማ እየተደረገ ነው። በJanuary 19 ምርጫው ይደረጋል። እንዲሁም የሽማግሌዎች ሰብሳቢ ከሽማግሌች መካከል ይመረጣል። በዚሁ ቀንም የ2019 የቤተ ክርስቲያን ሪፖርት የሚቀርብ ይሆናል። ለዚህ ፕሮግራም እየጸለየን እንድንቆይ አናሳስባለን።

**የአገልግሎት ጥሪ**

በተለያየ መስክ ለማገልግለ የምትፈልጉ ሽማግሌዎችን አነጋግሩ።

**የአርብ ፕሮግራም**

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ።

**እርስ በርስ እንተያይ**

የጀምርነውን ለሌሎች ወገኖቻችን የመደወል እና እርስ-በእርስ የመጠያየቁን ነገር አጥብቀን እንድቀጥል ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። በዚህ አገልግሎት እየተጋችሁ ያላችሁ ወገኖች እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

“ወደ ውጭም አውጥቶ፦ ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፦ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።” (ሐዋ. 16፡ 30-31)



⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
⇒ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፦
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| | | |
|---|---|---|
| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |

“እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ” ሉቃስ 2፡10

# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!




“ጐለመስሁ አረጀሁም፤ ጻድቅ ሲጣል፥ ዘሩም እህል ሲለምን አላየሁም።”
(መዝ. 37:25)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**January 12, 2020** | **ጥር 3፤ 2012 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| **ጸሎት** ........................... | ወንድም ረድኤቱ ካሳ |
| **አምልኮ**........................ | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| **ፕሮግራም መሪ** ............ | ወንድም ረድኤቱ ካሳ |
| **ቃል** ............................ | እሕት ሰናይት ከበደ |
| **ማጠቃለያ** ..................... | ፕሮግራም መሪ |

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

“የሁሉ ዓይን አንተን ተስፋ ያደርጋል፤ አንተም ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸዋለህ። አንተ እጅህን ትከፍታለህ፥ ሕይወት ላለውም ሁሉ መልካምን ታጠግባለህ።”
(መዝ. 145፡ 15-16)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አሰፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ሲሳይ መሸሻ | | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ኮከቤ አስረስ | | |
| ወ/ም ዘሪሁን/ዮሐንስ | | |
| ወ/ም አያሌው/ጸደቀ | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### እግዚአብሔር እረኛዬ ነው -- የሚያሳጣኝም የለም።

ባለፈው ሳምንት እንዳየነው መዝሙር 23 እግዚአብሔር የሕዝቡ እረኛ እንደሆነ ያስተምረናል። ከዚህም ተነስተን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር እረኝነት የሚያስተምረንን ሃሳቦች በጥቂቱ አይተናል። በተጨማሪም ዳዊት የራሱን ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን የግል ልምምድ መሰረት አድርጎ እግዚአብሔር ለእርሱ በግሉ እረኛው እደሆነ በመረዳት ይህንን መዝሙር እንደዘመረ ተመልክተናል። ዛሬ ደግም “የሚያሳጣኝም የለም” የሚለውን ሃሳብ እናያለን።

ዳዊት እግዚአብሔር እረኛው ስለሆነ የሚያሳጣው ነገር እንደሌለ ያውጃል። “የሚያሳጣኝም የለም” በሚለው ክፍል ውስጥ የምናገኘው አንዱ ሃሳብ በእግዚአብሔር ላይ መታመን ነው። እግዚአብሔር ለሕይወትና ለኑሮ የሚያስፈልገንን ሁሉ ይሰጠናል። እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሰው የሚያስገልገውን ሁሉ ካዘጋጀ በኋላ ነው ሰውን የፈጠረው። ሰው ፍጥረትን ሁሉ እንዲገዛና እንዲስተዳደር እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሙላት ውስጥ አስገባው። (ዘፍ. 1፡ 28-30) አሁንም ፍጥረትን ሁሉ የሚመግበው እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ጉዳይ ዳዊት ሲዘምር “የሁሉ ዓይን አንተን ተስፋ ያደርጋል፤ አንተም ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸዋለህ። አንተ እጅህን ትከፍታለህ፥ ሕይወት ላለውም ሁሉ መልካምን ታጠግባለህ” ይላል (መዝ. 145፡ 15-16)። እግዚአብሔር የፍጥረቱ ሁሉ መጋቢ ከሆነ ለልጆቹ ደግሞ የሚያስፈልጋቸውን እንደሚሰጥ ጥርጥር የሌለው ጉዳይ ነው። ጌታችን ባስተማረው የተራራው ስብከት “እንግዲህ፦ ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ... ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና” በማለት እግዚአብሔር የሚያሳጣን እንደሌለ አስተምሮናል (ማቴ. 6፡ 31-32)። የኛ ፋንታ የእግዚአብሔርን መንግስትና ጽድቅ መፈለግ ነው። እግዚአብሔር የሚስፈልገንን ሁሉ ይጨምርልናል። (ቁ. 33) ንጉስ ዳዊትም “ጐለመስሁ አረጀሁም፤ ጻድቅ ሲጣል፥ ዘሩም እህል ሲለምን አላየሁም” በማለት እግዚአብሔርን የሚፈልግ ፈጽሞ እንደማይጎድል ዘምሯል። ዳዊት ይህንን የዘመረው የሕይወት ዘመን ተመክሮውን ተመልክቶ ነው። በጉልምስና እና በእርጅና መካከል በትንሹ አርባ አመት አለ። በዚህ ረጅም የህይወት ተመክሮው ዳዊት የሚመስክረው ነገር በእግዚአብሔር ላይ ተደግፎ የሚያፍር ማንም እንደሌለ ነው።

ሁለተኛው “የሚያሳጣኝም የለም” የሚለው ሃረግ የሚያመለክተው በተሰጠን ነገር መርካትና ማረፍ እንዳለብን ነው። ይህ ክፍል በኪንግ ጄምስ የእንግሊዘኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም “I shall not want” ተብሏል። ሃሳቡ እግዚአብሔር እረኛችን ከሆነ ሙሉ በሙሉ በእርሱ እንደምንረካና እንደምናርፍ የሚያሳይ ነው። ሰው በቁሳዊ ነገር ፍጹም እርካታ ሊያገኝ አይችልም። እንዲሁም በቁሳዊ ነገር ለመርካት አይቻልም ምክንያቱም ቁሳዊ ነገር ከፊታችን እንደ ሚሸሽ ኢላማ ሁልጊዜ ደረስኩበት ስንል እልፍ የሚል በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር ግን ፍጹም የሚያሳርፍ አምላክ ነውና እግዚአብሔር እረኛው የሆነ ሰው የተሟላ፣ የረካና ያረፈ ሰው ነው። ሌላ የሚያረካ ምንጭ አይፈልግም። ነገር ግን የተቀበለው መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ውስጥ “ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ” ይሆንለታል (ዮሐ. 4:14)። እግዚአብሔር በእርሱ የምትደገፈውን ነፍስ ፈጽሞ በሰላሙ ይጠብቃታል (ኢሳ. 26:3)። እግዚአብሔር ሸክማቸው የከበደውን ሁሉ የሚያሳርፍ እውነተኛ እረፍትና እርካታን የሚሰጥ አምላክ ነው (ማቴ. 11:28፣ መዝ. 46:10፣ 1ጴጥ. 5፡7)። ወገኖቼ፦ ከእግዚአብሔር ውጪ ሙላትና እርካታ የለም። እርሱ እረኛችን ከሆነ የሚያሳጣን የለም።